# የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) እና የአማራ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (አዴፓ) በጋራ ለመሥራት ተሥማሙ።

January 11, 2019



የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) እና የአማራ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (አዴፓ) በጋራ ለመሥራት ተሥማሙ።

ሁለቱ ፓርቲዎች አሁን ያለውን የፖለቲካ አሠላለፍ ታሳቢ ያደረገ የሁለትዮሽ ውይይት በሥራ አሥፈጻሚዎቻቸው በኩል በአቶ ደመቀ መኮንን እና በዶ/ር ደሳለኝ ሠብሳቢነት ጥር 1 ቀን 2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተገናኝተው መክረዋል። ከአዴፓ 11 የሥራ አሥፈጻሚ አባላት የተገኙ ሲሆን በአብን በኩል 9 የሥራ አሥፈጻሚ አባላት በውይይቱ ላይ መገኘት ችለዋል።

በዚህም መሠረት ሁለቱ ፓርቲዎች፡-

1. በጸጥታ ጉዳይ
2. በሠላምና ደህንነት

[ ] 3. በልማትና የአማራ ህዝብ የጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመሥራት በሁለቱም ፓርቲዎች በኩል በተመረጡ ሥራ አሥፈጻሚዎች በኩል የጋራ ኮሚቴ አቋቁመዋል። ከሁለቱ ፓርቲዎች ሥራ አሥፈጻሚዎች የተመረጡት የጥምር ኮሚቴው አባላት ወደ ፊት ዝርዝር ጉዳዮችን የሚያሳውቁ መሆኑን አያይዘን እንገልጻለን!

አንድ አማራ ለሁሉም አማራ፣ ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ!

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)
አዲስ አበባ፣ ሸዋ!